የሲቪል መከላከያ　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　የትምህርት ሚኒስቴር

# በትምህርታዊ ተቋሞች ውስጥ
# ብሔራዊ የመከላከያ ልምምድ

**የካቲት** 14 **ቀን** 2017 **ዓ.ም.** ,י״ח בשבט תשע״ז

**ለወላጆች የተላከ ደብዳቤ**

የትምህርት ሚኒስቴርና የሲቪል መከላከያ (“ፒኩድ ሀዖሬፍ”) በየዓመቱ በእስራኤል አገር ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ትምህርታዊ ተቋሞች ውስጥ የመከላከያ ልምምድ ያካሂዳሉ። የመከላከያ ልምምዱ ትምህርታዊ ተቋሞች ለተለያዩ ድንገተኛና አስቸኳይ ሁኔታዎች ራሳቸውን ዝግጁ እንዲያደርጉ የሚያስችል **ወሳኝ ነጥብ** ነው።

**ዘንድሮ ልምምዱ የካቲት** 14 **ቀን** 2017 **ዓ.ም.** י״ח בשבט תשע״ז **በሁሉም ትምህርት ቤቶችና መዋዕለ ሕጻናት ውስጥ ከ**10:00 **እስከ** 12:00 **ሰዓት ድረስ ይካሄዳል።**

የዘንድሮ ልምምድ ተማሪዎች ክፍል ውስጥ እየተማሩ እያለ **የመሬት መንቀጥቀጥን** ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ነው። ባለፉት ቅርብ ጊዜያት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የመሬት መንቀጥቀጥ ስለመከሰቱ ሰምተናል። ይህም ሁኔታ እኛም ብንሆን ለዚህ ክስተት አስቀድመን ራሳችንን እንድናዘጋጅ ያስገድደናል። የትምህርቱ ሥርዓት ለአስቸኳይ ሁኔታዎች የሚያሳየው ከፍተኛ ዝግጁነት የእስራኤል ኅብረተሰብ ድንገተኛ ሁኔታዎችን በጥንካሬ እንዲቋቋም ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

ልምምዱ ሥራ ላይ የሚውለው የሲቪል መከላከያ በነደፈውና በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ የሚገኘው የመከላከያ ክፍል ባዘጋጃቸው መመሪያዎች መሠረት ነው። ልምምዱ የእናንተንና የልጆቻችሁን ደኅንነት ያጠናክራል፤ እንደዚሁም በድንገተኛ ሁኔታዎች ጊዜ የተማሩትን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይረዳል የሚል እምነት አለን።

የልምምዱ ስኬታማነት በልጆቻችሁና በእናንተ ሙሉ ተባባሪነት ላይ የተመረኰዘ ነው። ስለሆነም ከልጆቻችሁ ጋር ስለልምምዱ በየጊዜው ተነጋገሩ። ምክንያቱም በአስቸኳይ ሁኔታዎች ጊዜ የዝግጁነትን ጠቃሚነት እንዲረዱ ስለሚያደርግ ነው። ልምምዱ ልጆቻችሁ የደኅንነት ስሜት እንዲሰማቸውና የናንተንም ኃይል ያጠናክር ዘንድ የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን። ይህ እንዳለ ሆኖ ለትንንሽ ልጆቻችህ ማስረዳት ያለባችሁ የሚደረገው ልምምድ ነው እንጂ አደጋ የሚያስከትል አስቸኳይ ሁኔታ አለመሆኑን ነው።

የአስቸኳይ ሁኔታዎችን በጥሩ ሁኔታ መጋፈጥ የሚቻለው አስቀድሞ በጥሩ ሁኔታ በመዘጋጀት ነው። ስለሆነም የትምህርታዊ ተቋምና የቤተሰባችሁ ዝግጅት ትርጉም ያለው ነው። **አስቀድሞ የሚዘጋጅ ኅብረተሰብ አስቸኳይ ሁኔታዎችን በተቀላጠፈ መንገድ ይጋፈጣል።**

**ዝግጅትና በየጊዜው መለማመድ - በአስቸኳይ ሁኔታ ጊዜ በተገቢው ሁኔታ ለመጋፈጥ ዋነኞቹ ቁልፎች ናቸው!**

“ፒኩድ ሀዖሬፍ” ሊያገለግላችሁ ምንጊዜም ሊያገለግላችሁ ዝግጁ ነው:

ድረ-ገጽ፡ www.oref.org.il የመረጃ ማዕከል 104

ትምህርት ሚኒስቴር፡ shalitram@education.gov.il ስልክ 02-5603324

**ጄኔራል ዮኤል ስትሪክ**
**የሲቪል መከላከያ ዋና አዛዥ**

**ወ/ሮ ሚኻል ኮሄን**
**የትምህርት ሚኒስቴር ዋና ሥራ አስኪያጅ**